# *ማስታወቂያ*

## *በውጭ የሚኖሩ ግብር ከፋዮች የጣት አሻራ አሰጣጥ ጊዜን ስለማራዘም*

*የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን* የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን ከጣት አሻራ ጋር የማያያዝ ኘሮጀክት ከሐምሌ 7 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ በማካሄድ ላይ መሆኑ ይታወቃል።

በዚህ ኘሮጀክት ከሚታቀፉት ግብር ከፋዮች ውስጥ ባሁኑ ጊዜ ከሀገር ውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ግለሰቦች በሀገር ውስጥ ገቢ በሚያስገኙ ኢንቨስትመንቶች ወይም የንግድ ዘርፎች/ ቤት ማከራየትን ጨምሮ/፣ ሥራውን በተወካይ በማንቀሳቀስ ገቢ የሚያገኙ፣ ግብር እየከፈሉ ያሉ ወይም መክፈል ያለባቸውን ግለሰቦች ያካትታል፡

በጣት አሻራ በተደገፈ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሥርዓት በውክልና የጣት አሻራ መስጠት ስለማይቻል እስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም. ድረስ ወደ ሀገር ቤት በመምጣት የጣት አሻራቸውን መስጠት እንዳለባቸውና እስከዛው በተወካያቸው የሚሞላ ፎርም ተዘጋጅቶ የቀድሞውን የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር በመጠቀም አገልግሎት እንዲያገኙ ገልጾ እንደ ነበር አይዘነጋም።

ሆኖም በዚህ ጊዜ ውስጥ ወደሀገር በመምጣት አስፈላጊውን መረጃ የሰጡ ቢኖሩም፣ በተለያየ ምክንያት በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ወደ ሀገር መምጣት የማይችሉ ግለሰቦች እንዳሉና ጊዜው መራዘም እንዳለበት በተለያዩ ጊዜያት ጥያቄዎች እየቀረቡ እንደሆነ ታውቋል።

በዚሁ መሠረት ከተገልጋዮች የቀረበውን ችግር በመረዳት በውጪ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ብቻ ለአንድ ጊዜ የአሻራ መስጫው ጊዜ ለተጨማሪ ስድስት ወራት እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2003 ዓ.ም. ድረስ እንዲራዘም ተወስኗል። በመሆኑም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ ይህን ዕድል በመጠቀም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2003 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ ሀገር በመምጣት የጣት አሻራቸውን እና አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት መመዝገብ ይኖርባቸዋል።

እስከዚያው ድረስ ቀደም ሲል በተወካዮች የተሞላው ወይም በዚህ በማራዘሚያው ጊዜ ውስጥ በሚሞላው ፎርም አማካኝነት ተወካዮች የተለመደውን አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል።

የማራዘሚያ ጊዜ ቀድሞ የነበረውን የመለያ ቁጥር ያልወሰዱትን የማይመለከትና በዚሁ ሁኔታ ያሉት ማንኛውንም አገልግሎት ለማግኘት በሚጠይቁበት ጊዜ /ዕቃ ለማስመጣት፣ ንብረት ለመሸጥ፣ ለመለወጥ ፈቃድ ለማደስ ወዘተ... / አሻራቸውን ቀደም ብሎ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

በተጨማሪም የኩባንያ ባለአክስዮኖችን (Shareholders) እና ሕጋዊ ሰውነት ተሰጥቷቸው የተቋቋሙ ድርጅቶች (Private Limited Company, Share Company) ምዝገባው እንደማይመለከታቸው እንገልጻለን።